# Muslim evanglism



**Prepared by henok**

# ይሄ ትምህርት ለምን አስፈለገ ?

- እስልምና በዚህ ዘመን በቁጥር እየበዙ እና እምነቱም ከባህላዊነት ወደ አክራሪነት እየተቀየረ ስላለ።
- መጽሀፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን በብዙ ውሸቶች እየቀየጡ ወደ ትውልዱ እየቀላቀሉ ስላለ።( “ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል”)
- የክርስትና በሙስሊሞች ላይ የሚያደርገው ተጽእኖ በጣም አናሳ እናም በፖለቲካው ፣ በንግዱ ፣ በማህበራዊ ህይወት ላይ የእስልምና ተጽእኖ ጎልቶ እየታየ በመሆኑ።
- ያልሰለሙ ሙስሊሞች እየሰለሙ ያሉበት ወቅት ስለሆነ ትምህርቱ አስፈላጊ ነው። እየሰለሙ ያሉ ሙስሊሞች በኢትዮጵያ እየተበራከቱ ነው ይሄ ደግሞ ይዞት የሚመጣው መጥፎ የሆነ ውጤት አለ።

# በእስልምና የተለመዱ ቃላት

ሰላምታ ፡-  አስ-ሰላሙ አለይኩም / ሰላም ላንተ ይሁን  /

ለሀይማኖት  ስርአት መታጠብ ፡-  ውዱ

ወደ መካ ወይም መንፈሳዊ  ጉዞ ፡-   ሐጅ

መሀመድ መገለጥ ያየበት ዋሻ ፡-  ሂራ

የፍርድ ቀን ፡-  የሁማል -ቂያማ

ኢየሱስ ፡-  ኢሳ

ዮሴፍ ፡- ዩሱፍ

ሙሴ ፡- ሙሳ

ሄኖክ ፡- እድሪስ

ዳዊት ፡- ዳውድ

ኑህ ፡- ኖህ

ሱለይማን ፡- ሰለሞን


Muslim pop.
+200M
100-200M
50-100M
10-50M
5-10M
1-5M
500,000-1M
0-500,000

# statistics of muslim population in 2023

**Countries with the largest number of Muslims**

| Rank | Country | Muslims | Total population |
|---|---|---|---|
| 1 | Indonesia | **242,306,864** | 278,513,636 |
| 2 | Pakistan | **233,987,638** | 242,474,236 |
| 3 | India | **220,875,284** | 1,434,255,093 |
| 4 | Bangladesh | **157,723,076** | 173,703,828 |
| 5 | NIGERIA | **115,501,280** | 226,029,902 |
| 6 | Egypt | **108,120,247** | 113,452,515 |
| 7 | Iran | **88,558,529** | 89,453,059 |
| 8 | Turkey | **84,288,867** | 86,009,048 |
| 9 | ETHIOPIA | **45,901,474** | 127,859,260 |
| 10 | Iraq | **45,472,694** | 45,932,014 |

# comparision of major 3 religions over the years




**Sources**

- The 2022 Revision of World Population Prospects Department of Economic and Social Affairs, Population Division.
- Data Hub World Religion Projections
- WikipidiA Islam by country (Global Muslims percentage)
- Nations Geo

እስልምና መቼ ጀመረ ?

እስልምና መሰረት እና እምነት?

የእስልምና ጀማሪ ማነው?

**ስንት አይነት ሙስሊም አለ?**

# እስልምና የተጀመረው መቼ ነው?

- እስልምና የጀመረው በመህመድ እምነት እና አስተምሮ ላይ እንደሆነ ይታመናል።ነገር ግን ማስረጃዎቻቸው የሚያሳዩት እስልምና በመሃመድ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ሰዎች እንደሆነ ነው። አዳም ( 30፡30 ) ፣ ዙመር ( 39፡12 ) ፣ አብርሃም ( 2፡132 ) ፣ መሃመድ እንደሆነ ነው ስለዚህ የትኛውን ማመን አለብን?

- ለምሳሌ ፡- የዙመር ምዕራፍ ላይ «የሙስሊሞችም መጀመሪያ እንድኾን ታዘዝኩ፡፡» **39:12** tefsir - Ibn Al Kathir ሲፈስረው (እኔም) ታዝዣለሁ።

# እስልምና እና መሃመድ

- መሃመድ የእስልምና ጀማሪ መሆኑን ታሪክ እንዲሁም ቁራን ይናገራል ፡፡ «ለእርሱ ተጋሪ የለውም፡፡በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ፡፡**እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ**» (በል)፡፡ 6:163
- እስልምና በመሃመድ እምነት እና ልምምድ የተጀመረ ወይም የተመሰረተ ነው ማለት እስልምናን **ከመሃመድ ነጥሎ ማየት የማይታሰብ ነገር ነው**፡፡
- እስልምና በመሃመድ ልምምድ ላይ የተመሰረተ ከሆነ

# መሃመድ ለሙስሊሞች

- መሃመድ ማለት ለሙስሊሞች ከየትኛውም ነገር በላይ ነው ምክንያቱም መሃመድ የእስልምና ጀማሪ እና **የመጨረሻው** ነብይ ስለሆነ። በዚህ ምክንያት መሃመድ የነብያት ሁሉ መደምደሚያ ነው።

- Narrated Anas:-The Prophet (ﷺ) said "None of you will have faith till he loves me more than his father, his children and all mankind.“ sahih al-bukhari 15

አናስ እንደተረከው ነብዩ ( ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ "ከእናንተ ውስጥ ከአባቱ ፣ ከልጆቹና ከሰው ልጆች ሁሉ በላይ እስኪወደኝ ድረስ **እምነት የሚኖራቸው** የለም።"

# ቁርአን

- በሙስሊሞች እምነት መሠረት ቁርኣን **ፍፁም የሰው እጅ ያልገባበት** ከአላህ ዘንድ **በቀጥታ የወረደ መገለጥ** ነው፡፡ ይህንንም መገለጥ **‘ናዚል’** ወይም **‘ታንዚል’** በማለት ይጠሩታል፡፡ በ23 ዓመታት ውስጥ ለመሐመድ በጅብሪል አማካይነት የወረዱላቸው የአላህ ቀጥተኛ ንግግሮች ስብስብ እንደሆነም ያምናሉ፡፡ “ኡም አል ኪታብ” (የመፅሐፉ እናት) በመባል የሚታወቅ **ያልተፈጠረ** ነገር ግን አላህ **በነበረበት ጊዜ** ሁሉ ከርሱ ጋር የነበረ ጽሑፍ እንዳለና ቁርኣንም የዚያ ግልባጭ እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ (ሱራ 13፡39)

- ኻሊፋ ኡሥማን ታርሞ አንድ መልክ ያለው ቁርኣን እንዲዘጋጅ ካደረጉ በኋላ የመጀመርያዎቹን ጽሑፎች አቃጥለዋቸዋል። ( Sahih Al Bukhari 6:61:510 )
- ብዙ ሙስሊሞች አሁን በእጃቸው የሚገኘው የአረብኛ ቁርአን በ1924 ዓ.ም. ይህንን መልክ እንደያዘና ከዚያ ቀደም ከሚገኙት የእጅ ጽሑፎች በብዙ መልኩ የሚለይ መሆኑን አያውቁም።

- እስልምና በመሀመድ ህይወት ፣ ታሪክ እና ልምምድ ላይ የተደገፈ ስለሆነ ስለ መሀመድ የሚዘግቡልን መጽሀፍቶችን መጠቀም የግድ ነው። ስለ መሀመድ ህይወት ለመመዝገብ በቁርአኑ ብቻ የማይቻል ስለሆነ ወይንም ቁርአኑ በቂ ስላልሆነ ስለ መሀመድ ህይወት እና ልምምድ መመዝገብ (መሰብሰብ ) የተጀመረው **መሀመድ ከሞተ ከ 150-300 አመታት ውስጥ ነው።**

- የመሐመድ ቀዳሚው ግለ ታሪክ **ኢብን ኢስሐቅ** በተባሉ የኢራቅ ሰው **“ሲራት ረሱልአላህ”** (የአላህ መልእክተኛ ግለታሪክ) በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ ግለ ታሪክ **በ765** ዓ.ም. እንደተጻፈ የሚነገር ሲሆን በሁለት የእርማት ሥራዎች ውስጥ አልፏል፡፡ የመጀመርያውን እርማት ያደረጉት **አል-ባካኢ** የተሰኙ ደቀ መዝሙራቸው ነበሩ፡፡ በማስከተል ደግሞ **ኢብን ሒሻም** የተሰኙ ሰው **በ833** ዓ.ም. በማረም አሁን ያለውን መልክ ሰጥተውታል፡፡ ጉዳዩን ያጠኑት ሊቃውንት የኢብን ኢስሐቅ ሥራ ከሞላ ጎደል በኢብን ሒሻም እና በአል-ጦበሪ ጽሑፎች ውስጥ እንደሚገኝ የሚያምኑ ሲሆን ነገር ግን ዋና ጽሑፋቸው ጠፍቷል፡፡

በእስልምና የመጀመርያዎቹ ዘመናት አረቦች በዙርያቸው የሚገኙ ሕዝቦችን በመውረር ተጠምደው ስለነበር እስላማዊ ታሪኮችንና ትምህርቶችን በጽሑፍ ለማስፈር ጊዜ የነበራቸው አይመስልም።ስለዚህ ስለ መሀመድ ህይወት እና ልምምድ በተለያዩ ሰዎች ተጽፎ እና ተሰብስቦ ይገኛል።

- ibn ishaq was an **oral traditions** collector and also 8th century musslim **historian** and **hagiographer**




በኢብን ኢስሐቅ ተጽፎ በአልፍረድ ጉላውም የተተረጎመው ቀዳሚው
የመሐመድ ግለ ታሪክ ጥራዝ።

# የሃዲሳት ስብስብ (hadith collections)

ሃዲስ ማለት ለእስልምና እምነት እና ልምምድ መሰረት የሆነውን የመሃመድን ህይወት ልምምድ ከቁርዓን ተጨማሪ የሆነ መጽሃፍ ነው ።

ሀዲሳት ማለት የመሀመድ ቁርጥራጭ ታሪኮች እና ንግግሮች ሲሆኑ በሱኒ ሙስሊሞች የቀኖና ደረጃ የተሰጣቸው (authentic books) የሚባሉ ሀዲሳት አሉ እነዚህም 6 ናቸው ፦

- **ሳሂህ አል-ቡኻሪ** (870 ዓ.ም.፣ 256 ዓ.ም.) በኢማም መሐመድ ቢን ኢስማዒ አል-ቡኻሪ የተሰበሰበ ሲሆን 7,275 ሐዲሳት ተካተውበታል።
- **ሳሂህ ሙስሊም** (875 ዓ.ም.፣ 261 ዓ.ም.) - ሙስሊም ቢን ሐጃጅ አል-ነይሻፑሪ በተሰኙ ሰው የተሰበሰበ ሲሆን 9,200 ሐዲሳትን ይዟል።
- **ሱናን አቡ ዳውድ** (888 ዓ.ም.፣ 275 ዓ.ም.) - በአቡ ዳውድ ሸዓሥ አል ሲጂስታኒ የተሰበሰበ ሲሆን 4,800 ሐዲሳትን አካቷል።

- ጃሚ አል-ቲርሚዚ (892 ዓ.ም.፣ 279 ዓ.ስ.) - በመሐመድ ቢን ዒሳ አል ቲርሚዚ የተሰበሰበ ነው።
- ሱናን አን-ነሳዒ (915 ዓ.ም.፣ 303 ዓ.ስ.) – በአቡ አብዱልረህማን አን-ነሳዒ የተሰበሰበ ነው።
- ሱናን ኢብን መጃህ (887 ዓ.ም.፣ 273 ዓ.ስ.) - ኢብን መጃህ አል-ቀዝዊኒ በተባሉ ሰው የተሰበሰበ ነው።

# Sahih al-bukhari



ከአረብ ውጪ የሆኑና አዳዲስ ከሰለሙት አካባቢዎች የተውጣጡ ሙስሊም ሊቃውንት ተበታትነው የሚገኙትን በአፈ ታሪክ የሚነገሩትን የመሐመድን ድርጊቶችና ንግግሮ ማሰባሰብ ተያያዙ፡፡ ቡኻራ ከተሰኘችው **የኡዝቤኪስታን** ከተማ የመጡት **ኢማም አል-ቡኻሪ** ዋነኛ የሐዲስ ሰብሳቢ ነበሩ፤ ወደ 600,000 ሐዲሳትን ሰብስበው የነበረ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ተኣማኒ ናቸው ያሏቸውን 7,275 የሚሆኑትን ብቻ በመምረጥ የተቀሩትን አስወግደዋል፡፡




Sahih muslim (870 ዓ.ም.፣ 256 ዓ.ም)




# Jami At-Tirmidhi volume 6

# ሃዲስ በሁለት ይከፈላል

- **ኢስናድ**፡- የዘገባው ሰንሰለት(chain of narrators) ማን ማን በዘገባው እንዳሉ የሚያሳይ ነው።
- **መትን** ፡- refers to the **main text** or message of the hadith. የዘገባው ዋና ምንባብ

■ በተአማኒነት ደረጃ ሀዲሳት በሦስት ይከፈላሉ ፡-

- ✓ ሳሂህ ( sahih) ፡- ጠንካራ ናቸው
- ✓ ሃሰን ፡- ደህና
- ✓ ዶዒፍ ፡- የከማ



# መሃመድ ማነው ?

1.ውልደት 570

1.መገለጥ 610

መሐመድ

ሒጅራ 622

ሞቱ 632

# የመሀመድ ልደት

- የመሀመድ አባት **አብደላ አብዱልሙጠሊብ** ይባላሉ እናቱ **አሚና** ቢንት ወሒብ ትባላለች። መሀመድ ከመወለዱ በፊት አያቱ አብዱልሙጠሊብ አብደላን ጨምሮ 10 ልጆች ነበራቸው የአብደላ **እናት ዘምዘም** በውሀ ጉድጉዋድ ምክንያት **ከቆሬይሾች** በተነሳባቸው ተቋውሞ ምክንያት " የካባ ጌታ ( አላህ) ከእነዚህ ጠላቶቼ ቢያድነኝ እና አስር ወንድ ልጆችን ብወልድ አንዱን ልጄን እጣ በማውጣት ለመካ አላህ መስዋዕት አደርጋለሁ" ይሉ እንደነበር ይነገራል። በዚህም ምክንያት እጣው በመሀመድ አባት በአብደላ ላይ እንደወጣ እና ለዚህም ምትክ 100 ግመሎችን በመስጠት ህይወቱን እንዳዳኑ ይነገራል።

- ከብዙ ጊዜያት ቡኃላ መሀመድ ሳይወልድ **የ6 ወር** ህጻን እያለ አብደላ እንደሞተ ይነገራል። በመቀጠልም መሀመድ በ570 የተወለደ ሲሆን እናታቸው አሚና እስከሞተችበት ድረስ እሰከ 6 አመቱ ሀሊማ በተባለች ሴት ጋር በማደጎ ያደገ ሰው ነበር። ከዚያም መሀመድ በአያቱ አብዱልሙጠሊብ ጋር በእንክብካቤ ቢያድግም አያቱም በ8 አመት እድሜ እንደሞተበት ይነገራል።
- አባቱን ሳይወለድ ፣ እናቱ በ6 ዓመቱ ፣ አያቱ በ8 ዓመቱ የሞቱበት ሰው ፣በመሆኑ ከነዚህ ምክንያቶች የተነሳ የስነልቦና ጉዳት ደርሶበታል የሚሉ

# የቀጠለ.....

- መሃመድ ከ8 አመቱ ጀምሮ የአባታቸው ወንድም (አጎታቸው) ጋር መኖር ጀመር አጎቱን ለሌሎች ሰዎች በመቀጠር ( በእረኝነት) እስከ 12 አመቱ ድረስ ገንዘብ እያመጣ ያገለለው ነበር ፡፡ ከዚያን 12 ዓመት ሲሞላው ከ አጎቱ ጋር ለንግድ ወደ ሶሪያ  ሃገር በመንቀሳቀስ ይሰሩ ነበር፡፡ መሃመድ **ከአጎቱ ጋር ለ9 አመት** በንግድ ሰርቷል በንግድ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ከተለያዩ ሰዎችህ ጋር እንደሚገናኝ እና የመንፈሳዊ ጥያቄዎች ወደ እርሱ ሕይወት እንደመጣ ይወራል ፡፡
- በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ በ 21 አመቱ ከድጃን አገኛት ከድጃ ደግሞ ህብታም ነጋዴ ነበረች ለሷ 4 አመት ታማኝ አገልጋይ ሆኖ ካገለገለ ቡኋላ ታማኝነቱን አይታ ለጋብቻ ጥያቄ አቀረበችለት ፡፡ መሃመድም ይሄንን እድል በመጠቀም **በ 25 አመቱ** የ40 አመት ሴት ጋር ጋብቻ ፈጽመዋል ፡፡

የቀጠለ.....

**ከድጃን በማግባቱ መሃመድ ያገኘው ጥቅም ፦**

- ✓ በንግድ ከበረሃ ወደ በርሃ መንከራተት ትቷል
- ✓ ሃብታም ሴት ስላገባ ታዋቂነትን አትርፏል ።
- ✓ መንፈሳዊ ነገሮችን እንዲያሰላስል እድል አግኝቷል ።

- በዚህን ጊዜ መንፈሳዊ ነገር የማሰላሰል ፣ የመጾም ፣ የመጸለይ ጊዜ ያሳልፍ ነበር ። ለ6ወር የሚደርስ ጊዜም በዚሁ የ ጾም እና ጸሎት ጊዜ ሲያሳልፍ ነበር አዲስ መገለጥ የታየው።

# የመሃመድ መገለጥ

- መሃመድ ከደጃን ካገባ ቡሃላ መንፈሳዊ ነገር ለማሰላሰል ጊዜ ያገኘበት ወቅት ነበር ለጾም እና ለጸሎት ጊዜ የሰጠው እውነትን የመፈለግ ጥያቄ ውስጥ ስለ ነበረ ነው።
- በዚው በተለመደ ጸሎት ወስጥ እያለ **በ610** ማለትም **መሃመድ በ 40 ዓመቱ** አዲስ መገለጥ **በሂራ ዋሻ** ውስጥ ነበር ያየው። ወደ ሂራ ዋሻ እንዲገባ ምክንያቱ **መንፈሳዊ ረሃብ** ነበር
- ሂራ ዋሻ ማለት ከመካ 5km ወጣ ብሎ የሚገኝ ቦታ ነው በተራራው አናት ላይ ከመሬት 640 m ርቀት ላይ ይገኛል አሁንም ቦታው ይጎበኛል።


KOHLI
اقرا باسم ربك
الذى خلق
خلق الإنسان
من علق
غار حراء



የቀጠለ……

- መሃመድ መገለጡን ያየበት ወቅት የረመዳን ወር ተብሎ በሚጠራው ወር ላይ ነው፡፡ መገለጡን ሲቀበል የተገለጠለት አንድ ትልቅ መለአክ **ጅብሪል** ተብሎ የሚጠራ ነበር ፡፡ መላኩም መጣና በአረንጓዴ ሓር የተጠቀለለ ጽሁፍ ይዞ አንብብ ይለዋል መሃመድም ማንበብ አልችልም ይሉታል ጂብሪልም **መሃመድን ከመሬት ጋር በማጣበቅ** እስኪያልባቸው ድረስ በመያዝ ለሶስተኛ ጊዜ እንዲያነቡና ትእዛዝ ይሰጠዋል ፡፡ መሃመድም የሚያነበውን ሲጠይቀው ጅብሪል **ሱራ 96 ፡1-5**

# የመሃመድ መገለጥ ከማን ነበር ?

Sahihi al-bukhari

vol 1 : book 1 : num 2-3

አኢሻ እንደተረከቸው፡-አል ሀሪዝ ቢን ሂሻም ነቢዩን "መለኮታዊ ተመስጦ እንዴት ይመጣልሃል?" እንዲህ ሲል መለሰ፡- “በእነዚህ ሁሉ መንገዶች **መልአኩ አንዳንድ ጊዜ ደወል** በሚመስል ድምጽ ወደ እኔ ይመጣል፣ እናም ይህ ሁኔታ ሲተወኝ፣ **መልአኩ የተናገረውን አስታውሳለሁ**፣ እናም የዚህ አይነት መለኮታዊ ተመስጦ በጣም ይከብደኛል ፣ እና አንዳንድ ጊዜ መልአኩ በሰው አምሳል ወደ እኔ ይመጣል እና ያናግረኛል ፣ እናም የሚናገረውን ተረድቻለሁ እናም አስታውሳለሁ ። " አኢሻ (ረዲየላሁ ዐንሁ) አክላ፡- “በእውነት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጣም ቀዝቃዛ በሆነ ቀን በመለኮታዊ መንፈስ ሲነዱ አየሁ እና **ከግንባራቸው ላይ ላብ ሲወርድ ተመለከትኩ** (ተመስጦው

ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) መለኮታዊ ተመስጦ የጀመረው በመልካም ህልሞች መልክ ልክ እንደ ብሩህ የቀን ብርሃን እውን ሆነ እና ከዚያም የመገለል  ስሜት ነበረበት። ቤተሰቡን ለማየት ከመሻቱ በፊት ለብዙ ቀናት ያለማቋረጥ (አላህን ብቻ) ያመልክበት በነበረው የሂራ ዋሻ ውስጥ ለብቻው ይሄድ ነበር። የጉዞውን **ምግብ ይዞ ይሄድ ነበ**ር ከዚያም ወደ (ሚስቱ) ኸዲጃ ተመልሶ ምግቡን ይወስድ ዘንድ በሂራ ዋሻ ውስጥ እያለ በድንገት እውነቱ እስኪወርድበት ድረስ ይመጣ ነበር። መልአኩም ወደ እርሱ መጥቶ እንዲያነብ ጠየቀው። ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) “ማንበብ አላውቅም” ሲሉ መለሱ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አክለውም “**መልአኩ ያዘኝና ጨመቀኝና የምሞት እስኪመስለኝ ድረስ ረገጠኝ** ከዚያ በላይ መታገስ አልቻልኩም ከዛም ፈታኝ እና እንደገና እንዳነብ ጠየቀኝ እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩለት፡- “እንዴት እንደማላውቅ አላውቅም። አንብብ።' **ከዚያም እንደገና ያዘኝ እና እንደገና መታገስ እስኪያቅተኝ ድረስ ለሁለተኛ ጊዜ ጨመቀኝና የምሞት እስኪመስለኝ ረገጠኝና ለቀቀኝ** ። ከዚያም ፈታኝ እና እንደገና እንዳነብ ጠየቀኝ ነገር ግን እንደገና 'ማንበብ አላውቅም (ወይም ምን ማንበብ እንዳለብኝ) መለስኩለት። ? **ከዚያም ለሦስተኛ ጊዜ እየጨመቀ እና እየረገጠ ያዘኝና ገፋኝ** ከዚያም ፈታኝና ‹አንብብ በጌታህ ስም በዚያ በፈጠረው (ሁሉንም ያለውን) ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው።

አንብብ ጌታህም እርሱ ነው። በጣም ለጋስ." (96.1፣ 96.2፣ 96.3) ከዚያም የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) በተመስጦና በልባቸው በከባድ ድብደባ ተመለሱ። ከዚያም ወደ ኸዲጃ ቢንት ኩወይሊድ ሄደው **"ሸፈኝ! ሸፍኑኝ!"** ፍርሃቱ እስኪያልቅ ድረስ ሸፈኑትና ከዚያ በኋላ የሆነውን ሁሉ ነገራት እና "አንድ ነገር እንዳይደርስብኝ እፈራለሁ" አላት። ኸዲጃም "በፍፁም! በአላህ እምላለሁ አላህ አያዋርድህም። ከዘመዶችህና ከዘመዶችህ ጋር መልካም ግንኙነት ትኖራለህ፣ ድሆችንና ድሆችን ትረዳለህ፣ እንግዶችህን በልግስና ታገለግላለህ እና የሚገባቸውን መከራ የተቸገሩትን ትረዳለህ" ስትል መለሰች።

ከዚያም ኸዲጃ  የአክስቷ ልጅ ዋራቃ ቢን ኑፋል ቢን አሳድ ብን አብዱል ዑዛ ጋር ሸኘችው፤ እሱም ከእስልምና በፊት በነበረው ዘመን ክርስቲያን ሆኖ ጽሑፉን በዕብራይስጥ ፊደላት ይጽፍ ነበር። አላህ እንዲጽፈው የፈለገውን ያህል ከኢንጅል በዕብራይስጥ ይጽፍ ነበር። አዛውንት ነበሩ እና አይናቸውን አጥተዋል።

ኸዲጃ ዋራቃን እንዲህ አለች፡ "የወንድም ልጅህን ታሪክ ስማ የአክስቴ ልጅ!" ዋራቃ "የወንድሜ ልጅ ሆይ! ምን አይተሃል?" የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ያዩትን ሁሉ ገለጹ። ዋራቃ እንዲህ አለ፡- “ይህ አላህ **ለሙሴ የላከው ሚስጢርን የሚጠብቅ (መልአክ ጅብሪል) ነው።**

# መሀመድ መገለጥ ሲቀበል እንደ ግመል ያንኮራፋ ነበር

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፤ 27 ፡ 17

ነቢዩ በጂዕራና ሳሉ አንድ ሰው መጣ። ሰውየው ኻሉቅ ወይንም ሱፈራ በሚባል ሽቱ የተቀባ ካባ ለብሶ ነበር። ሰውየው ነቢዩን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፡- በኡምራየ ወቅት ላደርገው የሚገባ የሚያዙኝ ነገር ምንድን ነው? ከዛ በጨርቅ መጋረጃ በተጋረደ ቦታ ሆነው አላህ ለነቢዩ መልእክት ይሰጣቸው ጀመር። እኔም አላህ ለነቢዩ መገለጥ ሲሰጣቸው እንዴት እንደሚሆኑ ለማየት ጓጓሁ። ኡመርም እንዲህ አለኝ፡- ና! አላህ ለነቢዩ መገለጥ ሲሰጣቸው እንዴት እንደሚሆኑ ማየት ትፈልጋለህ? እኔም አዎን ስል መለስኩለት። ኡመርም የመጋረጃውን አንዱን ጎን አነሳልኝ፣ እኔም ነቢዩ ሲያንኮራፉ አየሁ። (ሌላ ተናጋሪ ኩርፊያው የግመል ይመስል ነበር ብሏል)

# መሃመድ መገለጥ ሲቀበል

- ያልበው ነበር
- መልዓኩ እንዲያነብ ያስገድደው ነበር
- መልዓኩ ይጨምቀው ነበር
- መልዓኩ ይረግጠው ነበር
- የሞት ፍርሃት ውስጥ ነበር
- አንዳንድ ጊዜ **መልዓኩ በደውል ድምጽ** ይገናኘው ነበር

# የደውል ድምጽ በእስልምና

Sahih muslim 24:5279 ፦

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ "**ደወል የሰይጣን የሙዚቃ መሳሪያ ነው።**" ( አቡ ሁሬይራ የዘገቡት ሀዲስ ነው)

የቀጠለ.....

Sahih muslim 25 : 5277

የአላህ መልዕክተኛ ሲናገሩ " መልአክ ደውልና ውሻ ይዘው ከሚጓዙ ጋር አብሮ አይሄድም። አቡ ሁሬይራ የተናገሩት ሃዲስ ነው።

# የቀጠለ.....

Sunnah abudawd 34:4218

ኢብን አዝ-ዙቤይር ሴት አገልጋዩን ሴት ልጁን ይዛ ወደ ኡመር እንድትሄድ ነገራት ልጅቷን እግሯ ደውል ያለበትን አልቦ እንዳደረገቻ ወሰደቻት። ኡመርም የአላህ መልዕክተኛ ከእያንዳንዱ ደወል ጋር ሰይጣን አለ ሲሉ ሰምቻለሁ አለና አልቦውን ቆራርጦ ጣለው።

ተፍሲር ኢብን ከሢር፤ ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 34-37

በዚህ በአል-ሒጅር ላይ ኢብሊስ ተረግሟል የሳኢድ ቢን ጁቤይር ( ለሙስሊም 78 ለቡኻሪ ደግሞ 147 ሰሂህ የሆኑ ሐዲሶችን በመስጠት በስሙ አስመዝግቧል።) ሲናገር **አላህ ኢብሊስን (ሰይጣንን) በረገመው ጊዜ "መልኩ ከመላዕክት ወደተለየ መልክ ተቀየረ፣ ድምጹም እንደ ደወል ድምጽ ሆነ።"** በዚህም ምድር ላይ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ የሚሰማ ማንኛውም የደወል ድምጽ የዛው የሰይጣን ድምጽ አካል ነው።

# የደውል ድምጽ የኢብሊስ ነው!

# ጉዞ ከመካ ወደ መዲና

- ከመካ 250 km ውስጥ ወደምትገኘው መዲና ስደት ያደረገው ሚስቱ ስለሞተች እናም በመዲና ካሉ የእርሱ ዘመዶች ደግሞም ተከታዩች ስለነበረው ነበር።
- መሀመድ **ሁለት ጉዞ እንዳደረገ ይነገራል**

1. **በመንፈስ አለም** **ቡራቅ** በምትባል ከበቅሎ አነስተኛና ከአህያ ተለቅ ያለ እንስሳ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቡራቅ የተባለውን እንስሳ **ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ** ጋር ሲደርሱ በድንጋይ በማሰር **ሚረጅ** በተባለ በመሰላል **እስከ 7 ሰማይ** በመውጣት ከነቢያት ጋር እንደተገናኙ ደግሞም ከሞቱበት በአላህ ፈቃድ በመነሳት ከመሀመድ ጋር ትውውቅ በማድረግ በሰለሞን ቤተመቅደስ ሰላት አብረው ሰግደው እንደነበር ያሳያል። ( እስልምናና የመሀመድ ታሪክ ገጽ 62:-64)

የቀጠለ……

**2**. ሁለተኛው ጉዞ ደግሞ ወደ መዲና ነበር የተጓዘው መሃመድ ተቃውሞ ስለደረሰበት እና የመሀመድን እምነት የተቀበሉ ሙስሊም የሆኑ ሰዎች በቦታው በመኖራቸው መሀመድ በመዲና ቃልኪዳን ከተከታዮቹ ጋር መግባቱ ይነገራል። 6 **ከዝራጅ** ከተባሉ ነገድ እንዲሁም በመቀጠልም 72 **ወንዶች እና 2 ሴቶች** ጋር ቃል ኪዳንን አደረጉ።

ቃል ኪዳኑም መሀመድ ጀነትን እንደሚሰጣቸው እነሱ ደግሞ ከጠላት እንደሚጠብቁት ነበር። ( መሀመድ ጀነትን መስጠት ይችላል ጀነቱ

# መሀመድ በመዲና የሰራቸው ስራዎች

- መንፈሳዊ መሪ በመሆን መንፈሳዊ ህብረትን  አቋቋመ
- ኡማ ወይንም እድር አቋቋሙ ይህም ሙስሊሞች ችግር ቢመጣ የሚረዳዱበት
- ሼሪያ ህግ አወጣ
- ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ላይ መሰገድ አለበት በማለት አዛን / የጸሎት ጥሪ / እንዲጀመር አስደረጉ

# የመሀመድ አሟሟት

መሀመድ የሞተው በ 632 ዓም በ62 ዓመታቸው ነበር የሞተውም እስልምናን በጦርነት ለማስፋፋት በማዋጋት ፣ በመምራት በእንዳንድ ቦታዎች በመቁሰል በውጊያ ስላሳለፈ ደክሞት እንደነበር እና በመጨረሻም ሚስቶቹን በማስፈቀድ ወደ አይሻ ቤት በመሄድ በበሽታ ታሞ በተኛበት ሞቶ እንደተገኘ ይነገራል።

የሙሐመድ አሟሟት እንዴት የነበረው በእስላማዊ ትውፊት ውስጥ በተጻፈው መሠረት ሙሐመድ በኸይበር አይሁድ ላይ ጦር አዝምቶ ወረራ በፈፀመበት ወቅት አንዲት አይሁዳዊት ሴት የተመረዘ ምግብ አብልታው ነበር። መርዙ አደገኛ ከመሆኑ የተነሳ ከምግቡ አብዝተው ከበሉት መካከል ቢሽር ኢብን አል በራ የተሰኘ ሰው ብዙም ሳይቆይ የሞተ ሲሆን ሙሐመድ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት በመርዙ ከተሠቃየ በኋላ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል። (Ibn Sa'ad's Kitab Al-Tabaqat Al-Kabir, English translation by S. Moinul Haq, Volume 2, pp. 251-252; al-Tabari's History, Volume 8, p. 124; Sunan Abu Dawud, Book 39, Number 4498; Sahih Muslim, Book 026, Number 5430; Sahih al-Bukhari, Volume 5, Book 59, Number 713)

የቀጠለ……

አይሻ እንዳወራችው፡- ነቢዩ በሞቱበት ህመም ሲታመሙ ሳሉ እንዲህ ብለው ይናገሩ ነበር፤ “አይሻ ሆይ! በኸይበር ከበላሁት ምግብ የተነሳ እስከ አሁን ህመም ይሰማኛል፣ በዚህ ሰዓት ግን **ከመርዙ የተነሳ የልቤ ስር እንደተቆረጠ** እየተሰማኝ ነው፡፡” (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 5፣ መጽሐፍ 59፣ ቁጥር 713)

# THE FIVE PILLARS OF ISLAM

# ( 5ቱ የእስልምና መሰረቶች )

Sahih al-bukhari

Volume 1 :Book 2 : Hadith 7

Narrated Ibn 'Umar:

Allah's Messenger (ﷺ) said: Islam is based on (the following) five (principles): 1. To testify that none has the right to be worshipped but Allah and Muhammad is Allah's Messenger (ﷺ). 2. To offer the (compulsory congregational) prayers dutifully and perfectly. 3. To pay Zakat (i.e. obligatory charity). 4. To perform Hajj. (i.e. Pilgrimage to Mecca) 5. To observe fast during the month of Ramada



Shahadah
Salat
Hajj
The 5 Pillars of Islam
Zakat
Fasting

1. **ሸአዳ ( የእምነት መግለጫ )** ፡-“Ash-hadu alla ilaha illaAllah, Wa ash-hadu anna Muhammadan Rasulu-Allah.” ትርጉሙም ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም መሀመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው ወይንም ነብይ ነው ማለት ነው። ይህንን **በቃል ሸምድዶ መያዝ** የአንድ ሙስሊም ግዴታ ነው። ይህንን ያስተማረው መሀመድ ብዙ አማልክትን የሚያመልኩ ስለሆኑ ነበር።

2. **ሶላት / pray / ፡-** በእስልምና አንድ ሙስሊም ማከናወን ከሚገባው መሰረታዊ ነገር **በቀን 5 ጊዜ መስገድ አለበት** በሚሰግድበትም ጊዜ ፊቱን ወደ መካ ጥቁር ድንጋይ ያለበት ጋር በማዞር ፣ በመታጠብ ወይም ንጹህ በመሆን "Ihdina al-sirata al-mustaqim." ወይንም በቀጥተኛው መንገት ምራን እያሉ ይሰግዳል። አንድ ሙስሊም አርብ ቀን ሲሆን ወይንም የጁምአ ቀን መልአክ በር ላይ አለ በጊዜ የሚመጡትን እና የማይመጡትን ይመዘግባል።

"አቡሁሬራ እንደተረከረው;- ነብዩ  እንዲህ አሉ **ሰላት በሴት ፣ በውሻ እና በአህያ** ምክንያት ይቋረጣል።"

Grade: Sahih (Darussalam)

Reference : Sunan Ibn Majah 950

In-book reference : Book 5, Hadith 148

English translation : Vol. 1, Book 5, Hadith 950

**3. ዘካት ( አስራት ) ፡-** በሙስሊሞች ዘንድ ትልኩ ኢባዳ / አምልኮ / ለሰዎች የሚደረግ እርዳታ ነው ይህንን የማያደርግ ሙስሊም የእምነቱን pillar እንደተቃወመ ይቆጠራል በተቻለው ሁሉ የተቸገሩትን መርዳት አለበት ነገር ግን አሁን ላይ ገንዘብ የሚውለው ለማን ነው ?

- ✓ ለእስልምና ማስፋፊያ
- ✓ ለቁርአን ትምህርት ቤቶች
- ✓ ሰዎችን ሸሀዳ ለማስያዝ
- ✓ በየመስጊዱ ላሉ ኢማሞች

**4. ጾም ( fasting ):-** በእስልምና የተለያዩ አይነት ጾሞች ቢኖሩም ዋናውና በህግ የተደነገገው የረመዳን ጾም ነው። ምክንያቱም ቁርአን ለመሀመድ መውረድ የጀመረበት ወር ስለሆነ ነው።

- የረመዳን ጾም ለ30 ቀን ነው የሚካሄደው
- ከጠዋት እስከ ማታ ምራቃቸውን እንኳን ሳይውጡ ይጾማሉ
- በሽተኞች እና ነፍሰጡር ሴቶች መጾም የለባቸውም ካሉበት ሁኔታ ሲወጡ የማካካሻ ጾም ይይጾማሉ።
- ህጻናት እና አሮጊቶች ጭምር ለመጾም አይገደዱም ።

5. **<u>የሀጅ ጉዞ ( መንፈሳዊ ጉዞ ) ፡-</u>** አንድ ሙስሊም

አቅሙ ከቻለ በአመት አንድ ጊዜ አለበለዚያ በተመቸው ጊዜ

ወደ መካ ወደሚገኝ ቅዱስ ስፍራ በመጓዝ መጎብኘት እና

ጸሎት ማድረግ አለበት፡፡





# ጥቂሩ ድንጋይ ምንድነው ?

- ጥቁሩ ድንጋይ **ከሰማይ ሲወርድ** እንደ ወተት ነጭ ነበር ነገር ግን የአደምን ልጆች  ሃጢያት  በመሸከሙ ጠቆረ ብለው ያምናሉ ።
- ጥቁሩን ድንጋይ መንካትና 7 ጊዜ ሮጥ ሮጥ ብለው መዞር ሃጢአትን ይደመሰሳል ።
- ጥቁሩ ድንጋይ  ሁለት ሚያይበት ዓይኖችና ሚናገርበት አፍ ተሰጥቶት በትንሣኤ ቀን ይፈርዳል ።
- የትኛውም ሙስሊም ስግደት በሚያቀርብበት ጊዜ ወደ ካባ እንዲሰግድ ታዟል ።

“ኢብን አባስ  እንዳስተላለፈው  የአላህ  መልእክተኛ    እንዲህ አለ፦- **ጥቁሩ ድንጋይ** ከሰማይ ነው የወረደው። ሲወርድም  እንደ ወተት ያለ ነጭ ሲሆን በአዳም ልጆች ኃጢአት ምንክያት ነው የጠቆረው።”

Jami` at-Tirmidhi 877

In-book reference

: Book 9, Hadith 70

English translation

Vol. 2, Book 4, Hadith 877

“አብደላህ ቢን ዑበይድ እንዳወሳው አንድ ሰው እንዲህ አለ፡- አቡ አበዱራህማን ሆይ ለምንድነው ሁል ጊዜ ሁለቱን ጠርዞች ብቻ ስትነካቸው የማይህ ? ብሎ ጠየቀው። እርሱም የአላህ መልእክተኛ እነርሱን **መንካትና 7 ጊዜ መዞር ኃጢአትን ይደመስሳል** ሲል ሰምቼዋለሁ አለ።”

Grade : Hasan (Darussalam)

Reference : Sunan an-Nasa'i 2919

In-book reference : Book 24, Hadith 0

English translation : Vol. 3, Book 24, Hadith 2922

የአላህ መልእክተኛ  እንዲህ አለ ፦

ጥቁር  ድንጋይ "በአላህ እምላለሁ! **አላህ በትንሣኤ ቀን የሚያየውን ሁለት ዐይን እና የሚናገርበትን  ምላስ ይሰጠዋል** በእውነት ለተነካው ሁሉ ይመሰክረዋል ።

Grade : Hasan (Darussalam)

Reference : Jami at-Tirmidhi 961

In-book reference : Book 9, Hadith 155

English translation : Vol. 2, Book 4, Hadith 961

የላሚትዋ ምዕራፍ 2 : 144 ፡-

ፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን። ወደምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን። ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ ወደ ካዕባ አቅጣጫ አዙር። **የትም ስፍራ ብትኾኑም ስትሰግዱ ፊቶቻችሁን ወደርሱ አግጣጫ አዙሩ**። እነዚያም መጽሐፉን የተሰጡት እርሱ ከጌታቸው ሲኾን እውነት መሆኑን ያውቃሉ። አላህም ከምትሠሩት ሥራ ዘንጊ


Likee
Likee ID: 556815953

# የሙስሊም እምነት

1. በአላህ የምናሉ / ወመንቱ ቢላሂ /
2. በመላዕክት መኖር ያምናሉ / ወመላዕክቲ /
3. በመጽሀፍት ያምናሉ / ወኩቱቢሂ /
4. በነቢያቶች ያምናሉ / ወረሱሂሉ /
5. በሰይጣን ያምናሉ / ወመንቱ ሼይጣን /
6. በመጨረሻ ቀን ያምናሉ / ወየኡመል አክር /
7. በአላህ ሁሉን ወሳኝነት ያምናሉ / በቀደር  ማመን

# በአላህ ማመን ( ወመንቱ ቢላሂ )

- በአላህ ማመን ማለት የሁሉ ነገር ፈጣሪ እንደሆነ ማመን ።
- አላህ ተጋሪ የለውም ብቸኛ ፈጣሪ እንደሆነ ማመን ።
- አላህ አይወልድም አይዋለደም የሚለውን ማመን ።

<< በል ፡- እርሱ አላሀ አንድ ነው ፡፡ አላህ የሁሉ መጠጊያ ነው ፡፡ **አልወለደም** ፣ **አልተወለደምም**>> ሱረቱ 112፡1-3

# በመላዕክት መኖር ያምናሉ ( ወመላዕክቲ )

መላእክት መንፈስ የሆኑ እና በአይን የማይታዩ እንደሆኑ ያምናሉ የተለያዩ የስራ ድርሻ እና ስም ያላቸው መላእክቶች አሉ

ከነዚህም ውስጥ የተወሰኑት ፡-

ጅብሪል ፡- የመገለጥ መልአክ ይባላል ( ሱረቱ አል-ነህል 16:102 )

ሚካኤል ፡- ምግብ የሚያዘጋጅ ነው ተብሎ ይታመናል

ረዋድ ፡- መልአከ ገነት ሲሆን የገነት ጠባቂዎች ሃላፊ ነው ይባላል ( ሱረቱ አል-ሙደሲር 74፡30)

ማሊክ ፡- የገሃነም ጠባቂዎች ሃላፊ ነው ይሉታል

እዝራኤል ፡- ሰው ሲሞት ነፍሱን የሚወስድ ነው ( ሱረቱ አል-ዓንዓም 6፡61 )

ናከር እና መንከር ፡- የሰውን እለተ እለት ተግባር የሚመዘገቡ ናቸው ( ሱረቱ አል-ቃፍ 50 ፡ 12 -18 )

የአላህ ዙፋን ተሸካሚ አሉ ብለው ያምናሉ ( ሱረቱ አል-ሓቃህ 69፡17)

# በመጸሃፍት ያምናለ

- በመጽሀፍቶች የምናምንባቸዉ ሙስሊሞች እነዚህ መጽሀፍቶች ከቁርአን በተጨማሪ ያሉ ናቸው።

    - ተውራት / ኦሪት /
    - ዛቡር / መዝሙር /
    - ኢንጅል / ወንጌል /
    - ፉርቃን / ቁርአን /

**ሱራ 5፡46** በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፡፡ **ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው፡፡**

**ሱራ 5 ፡ 47** የኢንጅልም ባለቤቶች **በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ**፡፡ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጸኞች እነርሱ ናቸው፡፡

ሱራ 2| 136| «በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም **በተወረደው** በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም

ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል

**የማንለይ ስንኾን አመንን**፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ፡፡

# በነብያቶች ያምናሉ

ሙስሊም 124,000 ነቢያት ወደ ሰዎች ከእግዚአብሄር ዘንድ ተሰተዋል ብለው ያምናሉ ከነዚህ ውስጥ 24 ሚደርሱ በቁራን ውስጥ አሉ ይላሉ ፡-

አዳም፣ እድሪስ፣ኑህ፣ኢብራሂም፣ ኢስሃቅ ፣ ኤሊየስ ፣ ኤልያሰእ ፣ ሉጥ ፣ ኢሳ ፣ እስማኤል ፣ ያቁብ ፣ ሙሳ ፣ ሱለይማን…….

# በሰይጣን ያምናሉ / ወመንቱ ሼይጣን /

ሁለት አይነት ሰይጣን እንዳለ ያምናሉ አንደኛው **ጂኒ** ሁለተኛው ደግሞ **ኢብሊስ** ይባላሉ።

ሰይጣን የወደቀበት መንገድ ቁራን ሲናገር አላህ አዳምን ፈጠሮን ስገዱለት አላቸው ሁሉ ሲሰግድ ሰይጥን ብቻ እኔ ከአዳም የምበልጥ ነኝ አልሰግድም አለ ከዚያን በዚህ ምክንያት አላህ እንደረገመው ይናገራል (ሱረቱ አል-አዕራፍ 7፡10-17)

**ጂኒ ሊሰልሙ የሚችል መናፍስት ናቸው።**

# በመጨረሻ ቀን ያምናሉ / ወየኡመል አክር /

በመጨረሻው ቀን ማመን ማለት ፡-

- ✓ በመቀስቀስ ማመን
- ✓ ሚዛን እንዳለ ማመን
- ✓ ጀነት እና ጀሃነም እንዳለ ማመን
- ✓ ሲራጥ እንዳለ ማመን

# በአላህ ሁሉን ወሰኝነት ያምናሉ / በቀደር ማመን /

- ሁሉ ነገር የተፈጠረው ነገር አላህ ወሰኖት እና ጽፎት እንደሆነ ማመን ነው

# ስንት አይነት ሙስሊም አለ ?

በአለማችን ላይ የሚታወቁ የእስልምና አይነቶች በጥቂቱ ፡-

- **ሱኒ**
- **ሱፊ**
- **ዋህባዊያን**
- አህመዲያንስ
- ሺዓይቶች

1. **ሱኒ** ፦ ሱኒ ማለት ሱና ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም **አካሔድ ፣ አረማመድ** ትክክለኛ መንገድ ማለት ነው። በቁጥራቸው ብዙ ሲሆኑ 90% የሙስሊም ክፍል ሱኒዎች ናቸው። የመሀመድን መንገድ አጥብቀው የሚከተሉ ናቸው።

2. **ሱፊ** ፦ ሱፊዎች ለአላህ ተለይቶ በመኖር ያምናሉ ወይም **ቋሚ ስፍራ ባለመያዝ** እንደ ምንኩስና መኖር ደግሞም እየዞሩ በማስተማር እስልምናን ለማስፋፋት የሚፈልጉ ናቸው።

3. **ዋህባዊያን** ፦ እነዚህ ቡድኖች በ17 ክፍለ ዘመን የተነሱ ሰዎች ናቸው እንቅስቃሴውን የጀመረው ሰው አብዱል **ወሒብ** የተባለ ሰው ነው። ወሒብ የእስልምና ምሁር ሲሆን በመካ አከባቢ የኖረ ሰው ነበር። በሳውዲ አረቢያ ታላቅ ተሐድሶን ያመጣ ሰው ነው። ወሒብ **ለዘብተኛ ሙስሊም ማየት አይፈልግም** ለዚህም ደግሞ ሙስሊሞች **ሰላት እንዲሰግዱ ፣ ኮፊያ እንዲያድርጉ ፣ ፂም እንዲያሳድጉ እንዲሁም ጂሐድን** ማንኛውም እስላም መፈጸም ያለበት እንደሆነ ይናገራል

# ቁርአን እና መጽሃፍ ቅዱስ መካከል ምን ልዩነት አለ ?




VS



# ቁርዓን

ቁርአን በሌላ መጠሪያው ፉርቃን በመባል የሚታወቀው መጽሀፍ ለእስልምና ሀይማኖት ከሰማይ የወረደ እና የጠራ እንከን አልባ ተደርጎ ይወሰዳል። በመሆኑም ቁርአን 114 ሱራዎች ( ምዕራፎች ) ሲኖሩት 6,236 አያዎች ( አንቀጾች) ወይም ቁጥሮች አሉት። ማንኛውም ሙስሊም አወቀም አላወቀም ከህጻንነቱ ጀምሮ በአረብኛ እንዲማሩ እና እንዲያጠኑ የደረጋል።

ቁርአን በገብርኤል አማካኝነት በመሀመድ ላይ መውረድ ጀመረ ተበሎ የሚታመነው በ610 AD እንደሆነ እስላማዊ መንጮች ይጠቁማሉ።

ቁርአን የተገለጠው ወይም የወረደው ለ23 ተከታታይ ዓመታት መካከል እንደሆነ ይነገራል። ይህም ማለት ከ610-632 ከመሀመድ በሒራ ዋሻ መገለጥ እስከ ሞት ድረስ ነው።

የመሀመድ ሞት ቡሃላ መገለጥ ወይም የቁርአን መውረድ የቆመ መሆኑ እስልምና በመሀመድ ላይ የተመሰረተ እምነት እንደሆነ ያሳያል።

# መጽሃፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቲያኖች ቅዱስ መጽሐፍ ነው። በእንግሊዝኛ bible የሚለው **"ቢብሊያ"** ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን "መጻሕፍት" ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ነቢያት፣ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ቋንቋዎች በ1500 ዓመታት ውስጥ ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎች የተጻፉ የተለያዩ መጻሕፍት ስብስብ ነው። በውስጡም 66 መጽሀፍት ሲገኙበት የብሉይ ኪዳን 39 አዲስ ኪዳን ደግሞ 27 መጻሕፍትን በውስጣቸው ይዘዋል። ይህ ማለት የክርስቲያኖች አምላክ በተለያዩ ሰዎች እንዲጻፍ ፈቅዷል።

መጽሐፍ ቅዱስ 1,189 ምእራፎችና 31,103 ቁጥሮች አሉት፡፡ የቁጥሮቹ ብዛት በተለያዩ ትርጉሞች ውስጥ በትንሽ መጠን ከዚህ ከፍ ወይም ዝቅ የሚልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ እነዚህ አከፋፈሎች በቀዳሚያን ጽሑፎች ውስጥ የማይገኙ ቢሆኑም ነገር ግን በመካከለኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ የኖሩ አይሁድና ክርስቲያን ሊቃውንት መጽሐፉን በቀላሉ ለማንበብ እንዲያመች በማሰብ በዚህ መልኩ ከፋፍለውታል፡፡

መጽሀፍ ቅዱስ በነገስታት ፣ በእረኞች ፣ በዓሣ አጥማጆች ፣ በካህናት ፣ በቀረጥ ሰብሳቢ ፣ በሐኪም ፣ በነብያት ወዘተ ቢጻፉም መልዕክቱን የተቀበሉት ግን ከአንድ ምንጭ ከእግዚአብሔር መሆኑን መላው ክርስቲያን ይስማሙበታል የምኑበታል፡፡

# አብርሃም ፣ እስማኤል እና ሎጥ

አብርሃም ከቤተሰቦቹ ጋር በሚኖርበት ጊዜ  ቤተሰቦቹ ጣኦት አምላኪዎች ስለነበሩ ጣኦታትን መሰባበሩ ቁርአን ይናገራል፡፡

<<(ዘወር ሲሉ) ስብርብሮች ደረጋቸው ፤ ኸለነሱ የኾነ  አንድ **ታላቅ (ጣዖት) ብቻ**  ሲቀር ወደ እርሱ ይመለሱ ዘንድ (እርሱን ተወው) >> ( ሱረቱ 21:58)

በዚህ የቁርአን ክፍል አብርሃም ከቅንአት ተነሳስቶ አደረገው ቢባል አንኳን ጥያቄ የሚያስነሳው ካጠፋቸው ጣኦታት መካከል  እንዱ ትልቁን ለምን አስቀረው? ሁሉንም ለምን  አላጠፋም? ሌላኛው ጥያቄ  ደግሞ አብርሃም ይህንን መፈጸሙ  ምንም አይነት አረጋጋጭ የለም  ዘፍ 12 ላይ አብርሀም ከቤተሰቡ ጋር ይኖር እንደነበር አንጂ ጣኦት ስለመስበሩ ምንም አይነት ፍንጭ የለም፡፡

# አብርሃም በተጠራ ጊዜ አባቱን ተከተለኝ ብሎአል ?

<< አባቴ ሆይ! እኔ ከዕውቀት ያልመጣህ ነገር በርግጥ **መጥቶልኛልና ተከተለኝ** ፤ ቀጥተኛውን መንገድ እመራሃለሁና >> ( ቁርአን ሱረቱ 19÷43)

ነገር ግን በመጽሀፍ ቅዱስ ዘፍ 12 ላይ አብርሃም ከዘመዶቹ ተለይ ከቤተሰቦቹ እንዲለይ በታዘዘው መሰረት ከቤተሰቡ እንደተለየ እና ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ እንደሄደ እንደወጣ ይናገራል። ይህ ማለት የአብርሃም መሪ እግዚአብሄር እራሱ እንደሆነ መጽሃፍ ቅዱስ ይናገራል ።

# የአብርሃም አባት አዘር ነው?

<< ኢብራሂም **ለአባቱ አዘር** ጣኦታትን አማልክት አድርገህ ትይዛለህን? >> (ሱረቱ 6÷ 74)

ይህ የቁርአን አንቀጽ በሁለት ምክንያቶች ከመጽሀፍ ቅዱስ ጋር ይጣረሳል አንደኛው አብርሃም አባቱ አዘር ነው? ወይስ ታራ? ሁለተኛው ደግሞ ጣኦትን እንዳያመልክ መውቀሱ የትኛው መጽሀፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ተቀምጧል?

# እስማኤል ነብይ ነው ተብሏል?

<< በመጽሀፉ እስማኤልንም አውሳ ፤ እርሱ ቀጠሮን አክባሪ ነበርና ፤ **መልዕክተኛ ነብይም** ነበር >>( ሱራ 19 ÷ 54)

በዚህ የቁርአን ምንባብ ውስጥ እስማኤል መልዕክተኛ እና ነብይ የነበረ መሆኑን መጽሀፍ ቅዱስ ተጽፎ ካለቀ ከ500 አመት ቡሃላ የመጣ (የወረደ) ቁርአን እንዴት መጽሀፍ ቅዱስ ላይ የሌለን ነገር ሊናገር ይችላል?

እስማኤል በመጽሀፍ ቅዱስ ምንም አይነት የነብይነት ኪዳን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሲቀበል ደግሞም መልዕክት ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ሲልክ አንመለከትም።

**Additionally :- አብርሃምና እስማኤል ካባን ( ጥቁሩን ድንጋይ) ገንብተዋል? ( ሱረቱ 22:26)**

# መንፈስ ቅዱስ ገብርኤል ነው?

<<እነዚያን ያመኑትን ለማረጋጋት ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር (ቁርኣንን) **ቅዱሱ መንፈስ** (ጂብሪል) እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው በላቸው። >>

( ሱረቱ 16:102)

ይህ የቁርአን ክፍል መጽሀፍ ቅዱስ ላይ የሌለን እውነት ትክክል ባልሆነ መረዳት እየሰጠ እንዳለ የሚያሳይ አንዱ ምንባብ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ገብርኤል አይደለም።

# የቁርዓኑ ኢሳ ኢየሱስ ነው?

በቁርአን ኢየሱስ ማለት ኢሳ እንደሆነ እና አላህ ለእስራኤል የሰጣቸው መልዕክተኛ እንደሆነ ይናገራል

በቁራን የኢሳ ታሪክ ምን ይናገራል መጽሃፍ ቅዱስስ ?

ሱራ 19:16-23

በመጽሐፉ ውስጥ መርየምንም ከቤተሰቧ ወደ ምሥራቃዊ ስፍራ በተለይች ጊዜ (የሆነውን ታሪኳን) አውሳ። ከእነሱም መጋረጃን አደረገች። መንፈሳችንምም (ጂብሪልን) ወደርሷ ላክን። ለእርሷም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰለላት። «እኔ **ንጹሕን ልጅ** ለአንቺ **ልሰጥሽ** የጌታሽ መልክተኛ ነኝ» አላት። (በጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ሆኜ አመንዝራም ሳልሆን ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል!» አለች። አላት «(ነገሩ) እንደዚህት ነው።» ጌታሽ « እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው። ለሰዎችም ታምር ከእኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው» አለ፤ (ነፋበትም)። ወዲያውኑም አረገዘችው። በእርሱም (በሆዷ ይዛው) ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች። ምጡም ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት። «ዋ ምኞቴ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩ። ተረስቼም የቀረሁ በሆንኩ» አለች።

የመጽሀፍ ቅዱሱ ኢየሱስ በገብርኤል አማካኝነት የተበሰረ እንጂ በገብርኤል አማካኝነት የተፈጠረ አይደለም! ገብርኤል ፈጣሪ ሆኖ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ አንመለከተውም። ነገር ግን ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ የተጸነሰ እንደሆነ ይናገራል።

በሱራ 19:23 መሰረት ዒሳ በዘንባባ ዛፍ ስር የተወለደ እንደሆነ ይናገራል። ነገር ግን መጽሀፍ ቅዱስ በሉቃ 2፥ 1-7 በከብቶች በረት በቤተልሔም እንደተወለደ ይናገራል።

# በህጻንነቱ እንደ ትልቅ ሰው ተናግሯል?

ሱረቱ መሪየም 19:28-30

«የሃሩን እኅት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም፡፡ እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም» አሏት፡፡

ወደርሱም ጠቀሰች፡፡ **«በአንቀልባ ያለን ሕጻን እንዴት እናናግራለን!» አሉ፡፡**

(ሕፃኑም) አለ «እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፡፡ መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል፡፡»

# ከጮቃ ወፍ ፈጥሯል?

ወደ እስራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል። (ይላልም)፡- «እኔ ከጌታዬ ዘንድ በተዓምር ወደ እናንተ መጣሁ። እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርፅ እፈጥራለሁ። በርሱም እተነፍስበታለሁ። በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል። በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፣ ለምጸኛንም አድናለሁ። ሙታንንም አስነሳለሁ። የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ። የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ተዓምር አለበት።»

ዮሐ 2፡11  ኢየሱስ ይህን በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም **የምልክቶች መጀመሪያ** በእርሱ አመኑ።

This beginning  of **miracles**  did  Jesus  in Cana of Galilee, and manifested forth his glory; and his disciples believed on him

# ኢየሱስ አልሞተም?

ሱረቱ 4፥157-158

«እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን» በማለታቸውም (ረገምናቸው)፡፡ አልገደሉትም አልሰቀሉትምም፡፡ ግን ለእነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ፡፡ እነዚያም በእርሱ ነገር የተለያዩት ከእርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፡፡ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፡፡ በእርግጥም አልገደሉትም፡፡

ቁርአን ኢየሱስ አልሞተም ብሎ ጠንካራ ሙግት ያቀርባል። በቁርአን አገላለጽም ኢየሱስን የሚመስል **ሰው ነው የተሰቀለው** ብለው ያምናሉ። በተጨማሪም ቁርአን ኢየሱስ ሳይሞት ወደ ሰማይ እንዳረገ ቁርአን ያስረዳል

ኢየሱስ በመጽሀፍ ቅዱስ እንደሚሞት ትንቢት እየተነገረለት እንደነበረ እንዲሁም በዛው መሰረት በእንጨት ላይ እንደሞተ እንደተነሳ እና ዳግም እንደሚመለስ ይናገራል። ስለዚህ **የቁርአኑ ዒሳ የመጽሀፍ**

ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 2

**8** በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ **ለሞትም**

ይኸውም **የመስቀል ሞት** እንኳ የታዘዘ ሆነ።

# የደህንነት ማረጋገጫ ( Assurance of salivation)

ስለ ደህንነት ዋስትና ከማውራታችን በፊት መስማማት ያለብን **ከሞት ቡሃላ ህይወት** እንዳለ ማመን ነው። ብዙ ሃይማኖቶት ከሞት ቡሃላ ህይወት እንዳለ ያምናሉ ነገር  ከሞት ቡሃላ ወደ ዘላለም ህይወት የሚያደርሳቸውን ዋስትና ስላልተቀበሉ በጥርጣሬ እና በስጋት ይኖራሉ ።

**ምሳሌ** ፡- አንድ አየር መንገድ ተሳፋሪ መድረሻውን በማወቅ ውይም ወዴት እንደሚሄድ እያወቀ ነገር ግን የመዳረሻውን ማረጋገጫ ትኬት ሳይዝ አይሄድም። ብዙ ሰው ጉዞ ጀምሯል ነገር ግን ወዴት እንደሚሄድ አያውቅም ስለዚሀ ያ ሰው ማድረግ ያለበሀ የምትሄድበት መንገድ ወዴት ነው የሚያደርሰኝ ፣ ትክክለኛ ነው ወይ? ብሎ መጠየቅ አለበት።

- የምንከተለው፣ የምንሄድበት መንገድ ወይም የምናምነው እምነት ወዴት እንደሚያደርሰን በግልጽ መናገር እና ማስረዳት አለበት ለዚህም ደግሞ ክርስትና ብቻ ነው ለዘላለም ህይወት ዋስትና ያለው ።
- Assurance of salivation is God given **confidence** for who believer in christ.
- ማረጋገጫ ማለት የምንከተለው  አምላክ ወይም  እምነት ለኛ የሰጠን confidence ነው።

# እስልምና ከሞት ቡሃላ ዋስትና አለው?

አል-ቃሪዓህ 101:6-8 " ሚዛኖቹ የከበዱለት ሰውማ እርሱ በምትወደድ ኑሮ ( ጀነት) ውስጥ ይሆናል። ሚዛኖቹ የቀለሉበት ሰውማ መኖርያውን ሃዊያህ( ሲኦል) ናት ።

- አንድ ሙስሊም ወደ ጀነት ከሚገባባቸው መንገድ አንዱ ሚዛኑ የከበደለት ሰው በመሆን ነው ። ይሄ የቁራን ክፍል ሲብራራ ኢብን አባስ ሲናገሩ ሙስሊም ለሆኑ እና ለሚያምኑ ሰዎች የተጻፈ እንደሆነ ይናገራል

"የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ሱሉ ሰማው " ማንኛቸውም መልካም ስራችሁ ከገሃነም እሳት ሊያድናችሁ አይችልም። እነርሱም የአላህ መልዕክተኛ እርስዋም ቢሆኑ በመልካም ስራዎት ከገሃነም እሳት አይድኑምን? አሉአቸው።**ነብዩ<<በፍጹም! አላህ ምህረቱን ካላበዛልኝ በስተቀር ስራዬ እኔን ከገነሃም እሳት አያድነኝም>>**

ሳሂህ አልቡካሪ ቅጽ 8:76:470

# ግጭት ወይስ እውነት?

ቁርአን ሚዛኑ የከበደለት ሰው ወይም መልካም በመስራት ሚዛኑ የከበደለት ሰው ነው ወደ ጀነት ሚገባው ሲለን መሃመድ ደግሞ ማንም በመልካም ስራ ሊገባ አይችልም ምክንቱም አላህ ምህረቱን ማብዛት አለበት ።

# የቀጠለ.....

## ሱረቱ መርየም 19

(66) ሰውም << በሞትኩኝ ጊዜ ወደፊት ሕያው ሆኜ (ከመቃብር) እወጣለሁን >> ይላል።

(67) ሰው ከአሁን በፊት ምንም ነገር ያልነበረ ሲሆን እኛ የፈጠርነው መሆኑን አያስታውስምን

(68) **በጌታህ እንምላለን ሰይጣናት ጋር በእርግጥ እንሰበሰባቸዋለን** ። ከዚያም በገሃነም ዙሪያ የተንበረከኩ ሆነው በእርግጥ እናቀርባቸዋን ።

(70) ከዚያም **ከየጭፍሮቹ ሁሉ** ከእነርሱ ያንን (እርሱ) በአልራህማን ላይ በድፍረት በጣም ብርቱ የሆነውን እናወጣለን ።

(71) ከዚያም እኛ እነዚያን እነርሱ በርሷ ለመግባት ተገቢ የሆኑትን እናውቃለን ።

(72) ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም። (መውረዱም) ጌታህ የፈረደው ግዴታ ነው።

ሱረቱ መርየምን ኢብን አባስ ሲያብራሩት እንዲህ ነበር ያሉት፡-

(ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም፡፡) **ነቢያትንና መልእክተኞችን ሳይጨምር** ከእናንተ ገሃነም ሳይገባ የሚድን አንድም ሰው የለም ማለት ነው፤ ((መውረዱም) ጌታህ የፈረደው ግዴታ ነው፡፡)

ይህም የግድ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡

## Mishkat al-Masabih 119

አቢ ደርዳዕ እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ አሉ" አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) አደምን ፈጠረ ፡ ከዚያም አደምን ከፈጠረው በኋላ የቀኝ ትከሻውን መታው ያኔም **ነጫጭ ጉንዳን የመሰሉ ዝርያዎች ወጡ** ፡ እንዲሁም የግራ ትከሻውን ሲመታው **ጥቁር ዝርያዎች ልክ ከሰል የመሳሰሉ ወጡ**

:በቀኝ በኩል ላሉት ቡድኖች እንዲህ አላቸው እናንተ ወደ ጀነት(ገቢዎች ናቸሁ) ፡ እኔም "አያገባኝም" እንዲሁም በግራ ትከሻው በኩል ላሉት ወደ ጀሃነም (ገቢዎች) ናቸሁ **እኔም አያገባኝም።**

- ጥቁር ሰዎች ለጀነት የተፈተሩ አይደሉም ደግሞስ አላህ ሰውን መፍጠሩስ ትክክል ነውን ?

# መጽሃፍ ቅዱስ ምን ይላል

1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5

**9 እግዚአብሔር ለቍጣ አልመረጠንምና**፥ በጌታችን  በኢየሱስ ክርስቶስ **መዳንን** ለማግኘት
ነው እንጂ።

10 የምንነቃም ብንሆን፥ የምናንቀላፋም ብንሆን፥ ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ
ስለ እኛ ሞተ።

1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2

3-4 **ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ** በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት

ሳሂህ አልቡካሪ ቅጽ 9:93:546

የአላህ መልክተኛ እንዲህ አሉ፡-ከእናንተ እያንዳንዱ በእናቱ ማህጸን ለአርባ ቀናት ይሰበሰባል ፣ከዛም በኋላ ለተመሳሳይ አርባ ቀን ወደ ረጋ ደምነት ይቀየርና ለተመሳሳይ አርባ ቀናት ወደ ቁራጭ ሥጋነት ይቀየራል።ከዛም በኋላ አላህ መልአክ ይልካል ፣አራት ነገሮችንም እንዲጽፍ ያዘዋል። የወደፊት ኑሮውን እድሜውን በኋለኛው ዘመን የተባረከ ወይንም እርጉም መሆኑን ይጽፋል ከዛ በሁዋላ ነፍሱን ይነፋበታል።በአላህ ከእናንተ መካከል አንዱ የገሐነምን ሰዎች ሥራ በእርሱና በገሐነም መካከል አንድ ክንድ እስኪቀር ድረስ ቢሰራ ከዛ አላህ መልአኩን አዞ ቀድሞ የጻፈውን የገነት ሰዎችን ስራ ይሰራል ገነትም ይገባል።ደግሞ አንዱ የገነት ሰዎችን ሥራ በገነትና በእርሱ መካከል አንድ ክንድ እርቀት እስኪቀር ድረስ ቢሰራ ከዛ በኋላ አላህ መልአኩን አዞ ቀድሞ የተጻፈበትን የገሃነም ሰዎችን ሥራ ይሰራና ገሃነም ይገባል።”

በመሆኑም መልካም ስራም ሆነ ክፉም ስራ ለጀነትም ሆነ ለገሀነም ምክንያት ሊሆኑ እንደማይችሉ ይልቁኑም የአላህ ቅድመ ውሳኔ መሆኑን መመልከት እንችላለን። ስለዚህም አንድ ሙስሊም ሙስሊም በመሆኑ ምክንያት ጀነት እገባለሁ ብሎ በእርግጠኛነት መናገር እንደማይችል ሳይታለም የተፈታ ነው።

# መጽሃፍ ቅዱስ ምን ይላል

1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5

**10** በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው፤ በእግዚአብሔር የማያምን
እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል።

**11** እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ
ነው።

**12** ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።

**13** የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለም ታምኑ ይህን

2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 1

**9** ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና **ጸጋ መጠን ነው** እንጂ **እንደ ሥራችን መጠን አይደለም**፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፥

**10-11** አሁን ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቶአል። እርሱ ሞትን ሽሮአልና እኔ ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን በተሾምሁበት **በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቶአል።**

# በሙስሊሞች የሚነሱ ጥያቄዎች

- ✓ ኢየሱስ አምላክ ከሆነ እኔ አምላክ ነኝ አምልኩኝ ያለበትን ስፍራ አሳዩን ?
- ✓ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው የሚለው የቱጋር ነው ?
- ✓ ክርስቶስ አምላክ ከሆነ ለምን የዮሐንስ ወንጌል 5፡30 ( እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም ) አለ ?
- ✓ ክርስቶስ አልተሰቀለም አልተገደለም ሱረቱ 4፡157 በተጨማሪም የበርናባስ ወንጌል ይናገራል።

# “የበርናባስ ወንጌል”

- ብዙ ሙስሊሞች ለመከራከሪያነት ከሚጠቀሙባቸው ምንጮች ውስጥ አንዱ የበርናባስ ወንጌል የተሰኘው መሃፍ ነው ፡፡
- የበርናባስ ወንጌል በመካከለኛው ዘመን **በጣልያን አገር በአንድ ሙስሊም የተጻፈ** የፈጠራ ጽሑፍ ሲሆን ከአንደኛው ክፍለ ዘመን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፡፡ ሙስሊም ወገኖች ብዙ ጊዜ “**የበርናባስ ወንጌል**” የተሰኘውን ጽሐፍ ከበርናባስ መልዕክት ጋር ሲያምታቱ ይስተዋላል፡፡


THE
GOSPEL
of
BARNABAS

## የበርናባስ ወንጌል የአንደኛው ክፍለ ዘመን ጽሑፍ አለመሆኑን የሚያሳዩ ብዙ ነጥቦች በውስጡ ይገኛሉ፡-

“ክርስቶስ” የሚለው የግሪክ ቃል እና “መሲህ” የሚለው የእብራይስጥ ቃል “የተቀባ” የሚል ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በአንደኛው ክፍለ ዘመን የኖረ የትኛውም አይሁዳዊ ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም እንዳላቸው ያውቃል። በርናባስን የመሰለ የግሪክ ቋንቋ ከሚነገርባት **ከአሌክሳንደርያ የመጣ አይሁዳዊ** ይህንን ቀላል እውነታ ይዘነጋል ተብሎ በፍፁም ሊታሰብ አይችልም። ነገር ግን የበርናባስ ወንጌል ገና ሲጀምር ኢየሱስን “ክርስቶስ” ብሎ የጠራው ሲሆን ነገር ግን ምዕራፍ 42 ላይ ኢየሱስ መሲህ መሆኑን መካዱን ይነግረናል በኢሳያስ መጽሃፍ ላይ እንዳለው በይሁዳ የሚጮህ ድምጽ ነኝ ብሎ ሲናገር ያሳየናል ።ስለዚህ 1ኛ ክፍለዘመን ላይ ያለ ጽሁፍ አይደለም።

የበርናባስ ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ አልሞተም አልተሰቀለም የሚል ብቻ ሳይሆን በምትኩ የሞተው ይሁዳ እንደሆነ ተናግሯል፡፡( የበርናባስ ወንጌል ምዕራፍ 2፡5 ወይም 217)

ሌላኛው በመጽሃፉ ምዕራፍ 3 ላይ ሄሮድስ  እና ጲላጦስ በአንድ ዘመን  የይሁዳ ገዢዎች እንደነበሩ ይናገራል፡፡ ነገር  ግን ሄሮድስ ከ37-4 ዓ.ዓ.  ይሁዳን ብቻውን  የገዛ ሲሆን  ጲላጦስ  ደግሞ  ከ26-36 ዓ.ም. ነበር የገዛው፡፡ በርናባስ ይህንን የታሪክ ቅጥፈት ሊፈፅም የሚችልበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡

በምዕራፍ 20-21 ላይ ኢየሱስ በጀልባ ወደ ናዝሬት ከተማ እንደሄደና የከተማይቱ ጀልባ ቀዛፊዎች እንደተቀበሉት ይናገራል፡፡ ነገር ግን ናዝሬት ከገሊላ ባሕር 14 ኪ.ሜ. ርቃ በተራሮች ተከባ የምትገኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚሁ ቦታ ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ከተማ ሽቅብ እንደወጣ የሚናገር ሲሆን ይህም ሌላ **ጂኦግራፍያዊ** ስህተት ነው፡፡ የቅፍርናሆም ከተማ አቀማመጥ ከናዝሬት በላይ ከፍታ ላይ ሳይሆን ታች የገሊላ ባሕር አጠገብ ነው፡፡ ኢየሱስ በተደጋጋሚ ወደ እነዚህ ከተሞች በመሄዱ ምክንያት ደቀ መዛሙርቱ በሚገባ ያውቋቸዋል (ማቴዎስ 2:23፣ 4:13፣ 8:5፣ 11:23፣ 17:24፣ 21:11፣ 26:71፣ ሉቃስ 4:16 )፡፡ ነገር ግን የበርናባስ “ወንጌል” ጸሐፊ ይህንን ስህተት በመስራት አጭበርባሪነቱን ይፋ [illegible]

ቁርአን ሰባት ሰማያት ብቻ እንዳሉ የሚናገር ሲሆን (ሱራ 17፡44) የበርናባስ ወንጌል ግን ዘጠኝ መኖራቸውን ይናገራል (ም. 178)።

የበርናባስ ወንጌል የመካከለኛው ዘመን ፈጠራ መሆኑን የሚያሳዩ ጠቋሚ ምልክቶች በውስጡ ይገኛሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ኢዮቤ **ልዩ በየ ሃምሳ ዓመቱ እንዲከበር ትዕዛዝ የተሰጠ ሲሆን** (ዘሌዋውያን 25፡10-11) በ1300 ዓ.ም. የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ **የነበሩት ቦኒፌስ ስምንተኛ በየ መቶ አመቱ እንዲከበር አውጀ**ው ነበር። ነገር ግን ቀጣዩ ጳጳስ ክሌመንት አራተኛ አዋጁን በመሻር ተመልሶ በየ ሃምሳ ዓመቱ እንዲከበር ስላወጁ በ1350 ዓ.ም. ተከብሯል።የበርናባስ ወንጌል ግን ይህንን የጳጳሱን የተሳሳተ አዋጅ በመቀበል በምዕራፍ 82 ላይ የኢዮቤ ልዩ በዓል በየ መቶ ዓመቱ እንደሚከበር ይናገራል። ይህም መጽሐፉ በመካከለኛው ዘመን የተጻፈ ስለመሆኑ ትልቅ ማስረጃ ነው።

ይህ መጽሐፍ የመካከለኛው ዘመን ፈጠራ መሆኑን የሚያመለክተው ሌላው ነጥብ ከዘመኑ ጸሐፊ ከዳንቴ ሥራዎች ላይ የተቀዱ ሐሳቦች በውስጡ መገኘታቸው ነው። ለምሳሌ  ያህል ከገነት በፊት ዘጠኝ ሰማያት መኖራቸውን ጸሐፊው ከዳንቴ ልበ ወለድ ላይ መውሰዱ ግልፅ ነው (ም. 178)።

የበርናባስ ወንጌል ቀዳሚያን የእጅ ጽሑፎች በጣልያንኛና በእስፓኒሽ የተጻፉ ሲሆኑ ምርመራ ተደርጎባቸው ከአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ የተጻፉ መሆናቸው ተረጋግጧል። እውነተኛው በርናባስ ጽፎት ቢሆን ኖሮ **በእብራይስጥ፣ በግሪክ ወይንም ደግሞ በአረማይክ ነበር መጻፍ የነበረበት።**

የጠለቀ ዕውቀት የሌላቸው ሙስሊሞች ይህንን መጽሐፍ እንደ ተዓማኒ ወንጌል ቢያራግቡትም ነገር ግን ጉዳዩን በጥንቃቄ ያጠኑ ሙስሊም ሊቃውንት ሳይቀሩ ሐሰተኛ መጽሐፍ መሆኑን ዕውቅና ይሰጣሉ።

# ኢየሱስ አምላክ ነኝ ብሏል?

- በመጀመሪያ በምድር ላይ የተለያዩ አምላክ እኝ የሚሉ ሰዎች ተነስተዋል ሁሉም ኝ ትክክለኛ ናቸው ማለት አይደልም ይልቅ አንድን አምላክ “አምላክ ነው” የምንለው አምላክ ነኝ ስላለ አይደለም **የአምላክነት(የመለኮት) ባህርይ** ስለታየበት እንጂ አምላክ ነኝ ስላለ አይደለም።

## በቁርአኑ የአምልክነት መመዘኛ እንኳን ኢየሱስ አምላክ ነው

- ቁራዓኑ አላህን **አልፋ እና ኦሜጋ ብሎታል**። ሱራ 57:2-3 :- የሰማያትና የመደር ንግስና የእርሱ ብቻ ነው። ሕያው ያደርጋል፣ይገድላልም። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው። **እርሱ ፊትም ያለ ፣ ኋላም ቀሪ** ፣ ግልጽም ስውርም ነው እርሱም ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው።

- በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቶስ አልፋ እና ኦሜጋ ተብሏል።

የዮሐንስ ራእይ 1

**8** ያለውና የነበረው የሚመጣውም **ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ**፡- አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።

- ሌላኛው መመዘኛ ደግሞ አላህ **በመጨረሻው ዘመን ሊፈርድ** ይመጣል

ሱራ 22:56-57 ፦ በዚያ ቀን ንግስናው የ አላህ ብቻ ነው። በመካከላቸው ይፈርዳል። እነዚያ ያመኑት መልካም ስራዎችንም የሰሩት በመደሰቻ ገነቶች ወስጥ ናቸው። እነዚያ የካዱት በአንቀጾቻችንም ያስተባበሉት እነዚያ ለእነርሱ አዋራጅ ቅጣት አላቸው።

- በመጨረሻ ዘመን ኢየሱስም ሊፈርድ ይመታል በሎ ይናገራል።

የማቴዎስ ወንጌል 25

**31** የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ  ከእርሱም ጋር ቅዱሳን  መላእክቱ  ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ  በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤

**32** አሕዛብም  ሁሉ  በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥

2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4

**1** በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፥ በመገለጡና በመንግሥቱም እመክርሃለሁ፤

# እየሱስ ራሱ አምላክ ነኝ ብሏል !

የዮሐንስ ወንጌል 13

**13** እናንተ መምህርና **ጌታ** ትሉኛላችሁ፤ **እንዲሁ ነኝና** መልካም ትላላችሁ።

# ኢየሱስ ከአብ ያንሳል?

የዮሐንስ ወንጌል 5

**19** ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፥
አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ **ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም**
**አይችልም**፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና።

..............

**30** **እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም**፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ
ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።

የዮሐንስ ወንጌል 5

**17** ኢየሱስ ግን፦ አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው።

**18** እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ደግሞ ራሱን **ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ**፦ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፥ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።

የዮሐንስ ወንጌል 10

**30** እኔና አብ **አንድ** ነን።

ክርስቶስ አንሳለው እያለ አንድ ነን ወይም
አምላክ ነኝ ማለቱ አይጋጭም ?

# 2 አይነት መገዛት( ማነስ ) አለ

- በማንነት ማነስ ( ontological subordination)
- በተግባር ወይም በስራ ማነስ ( functional subordination )

ክርስቶስ እየሱስ ከራሴ አንዳቸ ማድረግ አይቻለኝም ማለቱ ontological subordination ሳይሆን የሚያሳየው functionally  እራሱን ማስገዛቱን የሚያሳይ ነው።

# ለሙስሊሞች ወንጌልን እንዴት እናደርስ?

- ፍርሃትን ማስወገድ አለብን ወንጌልን ለማድረስ እንቅፋት ከሚሆኑብን ነገሮች ወስጥ አንዱ ፍርሃት ነው። ስለዚህ ፍርሃትን ለማስወገድ ደግሞ ስለነሱ ማወቅ እና በተቻለ መጠን ያንን እውቀት መለማመድ አለበን ። ለምሳሌ ፡- ሰው እባብን ይፈራል ነገር ግን እባብን በሚገባ ብናውቀው ፤ ስንት አይነት የእባብ ዝርያ አለ? ፤ የእባብን ባህሪያት ብናውቅ እና ያንን እውቀት ብንለማመድ **ፍርሃት ከውስጣችን** ይወጣ ነበር።

- ቃላትን መምረጥ ወይም እነሱን ሊያስቆጡ የሚችሉ ያልተገቡ ቃላትን መምረጥ እና እውነትን በፍቅር መናገር አለብን ምክንያቱም እነሱን በሚያስቆጣ መልኩ እየተናገርናቸው እነሱን መስበክ አይቻልም ።
- Pcs ( pray ,care and share ) ስልትን በመጠቀም ወንጌልን ለሙስሊሞች ማድረስ